# ሶሰቱ መሰረታዊ መርሕ

## ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ቡይማን አትተሚሚ

### የሶላት ሸርጦች
### እና የሶላት ዋጂቦች
### የሶላት ማእዘኖች

# الأصول الثلاثة والقواعد الأربعة
## ويليه شروط الصلاة وواجباتها وأركانها



بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

አላህ ርህራሄውን ይስጥህና አራት ጉዳዮችን አጠናቀን መረዳት ግዴታችን መሆኑን ዕወቅ። እነሱም:-

አንደኛ– (ዕልም) ሲሆን ይህም አላህን ነቢዩንና የእስላምን ሃይማኖት (ዲን) በማስረጃ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ማወቅ፤

ሁለተኛ– ይህን ዕውቀት ተግባራዊ ማድረግ፥

ሦስተኛ– ይህን ዕውቀት ማስራጨትና ለዚህም ጥሪ (ደዕዋ) ማድረግ፤

አራተኛ– ዕውቀቱን በመተግበሩና በማስራጨቱ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በትዕግስት መቋቋም ናቸው። ለዚህ ማስረጃው ቀጥሎ የተመለከተው የአላህ ቃል ነው :-

﴿ وَٱلْعَصْرِ ﴿١﴾ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لَفِى خُسْرٍ ﴿٢﴾ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلْحَقِّ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلصَّبْرِ ﴿٣﴾ ﴾

«በጊዜያቱ እምላለሁ፤ ሰው ሁሉ በእርግጥ በኪሳራ ውስጥ ነው። እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሰሩት፤ በውነትም አደራ የተባሉት ፤ በመታገሥም አደራ የተባሉት ብቻ ሲቀሩ።»[1]

---

1. አል–ዐስር(103):1–3

ኢማም አሽ–ሻፊዒ(ረዐ) ይህን የቁርአን ምዕራፍ አስመልክተው ሲናገሩ «አላህ ለፍጡራኑ ከዚህ ምዕራፍ ውጭ ሌላ ተጨማሪ አስረጅ ያላስተላለፈ (ያላወረደ) ቢሆን ኖሮ እንኳ ይህ ብቻ በቂ በሆን ነበር» ብለዋል።

ኢማም አል–ቡኻሪም(ረዐ) «ዕውቀት ከቃልም ሆነ ከተግባር ይቀድማል። ለዚህ ማስረጃው ቀጥሎ ያለውና ከቃልና ከተግባር ዕውቀትን(ዕልምን) ያስቀደመው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው ብለዋል:- «فاعلَمْ أنهُ لا إلهَ إلا الله واستغفِرْ لذَنبكَ»

«እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ ስለ ስሕተትህም፣ ለምእመናንና ለምእመናትም ምሕረትን ለምን!..[2]

አላህ ይዘንልህና እያንዳንዱ ሙስሊምና እያንዳንዷ ሙስሊም ቀጥሎ የተመለከቱትን ሶስት መሰረተ ሐሳቦች መገንዘብና በተግባር መተርጎም ግዴታው ወይም ግዴታዋ መሆኑን ዕወቅ። እነሱም:-

አንደኛ– አላህ ፈጥሮናል። ሲሳይ ሰጥቶን መግቦናል። እንዲሁ በከንቱ አልተወንም። መልክተኛውን ወደኛ ልኮ የታዘዘው ሰው ጀነት እንዲገባ በትዕዛዙ ላይ ያመጸ ሰውም ወደ እሳተ ገሐነም እንዲገባ አድርጓል። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ إِنَّآ أَرْسَلْنَآ إِلَيْكُمْ رَسُولًا شَٰهِدًا عَلَيْكُمْ كَمَآ أَرْسَلْنَآ
إِلَىٰ فِرْعَوْنَ رَسُولًا ﴿١٥﴾ فَعَصَىٰ فِرْعَوْنُ ٱلرَّسُولَ
فَأَخَذْنَٰهُ أَخْذًا وَبِيلًا ﴿١٦﴾ ﴾ سورة المزمل: ١٥،

---

2. ሙሐመድ (47):19

«እኛ በናንተ ላይ መስካሪ መልክተኛን፣ ወደናንተ፣ ላክን፤ ወደ ፈርዖን መልክተኛን እንደላክን። ፈርዖንም መልክተኛውን አመጠ፤ ብርቱ መያዝንም ያዝነው።»[3]

ሁለተኛ – አላህ(ሱወ) ባለሟል መልአክም ይሁን ተልዕኮ የተሰጠው ነቢይ፣ ማንንም ፍጡር ከርሱ በማጋራት(በማሻረክ) ማምለክን በፍጹም አይቀበልም። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَأَنَّ ٱلْمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُواْ مَعَ ٱللَّهِ
أَحَدًا ﴾ سورة الجن : ١٨.

«እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው፤ (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ፤ (ማለትም)።»4

ሶስተኛ– የአላህን መልክተኛ የታዘዘና የአላህን አንድነት ያረጋገጠ ሰው፤ የቅርብ ዘመድ ቢሆን እንኳ አላህንና መልክተኛውን የሚቀናቀነውን ሰው በወዳጅነት መያዝ አይፈቀድለትም። ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ لَّا تَجِدُ قَوْمًا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ يُوَآدُّونَ مَنْ
حَآدَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَوْ كَانُوٓاْ ءَابَآءَهُمْ أَوْ أَبْنَآءَهُمْ
أَوْ إِخْوَٰنَهُمْ أَوْ عَشِيرَتَهُمْ ۚ أُوْلَٰٓئِكَ كَتَبَ فِى قُلُوبِهِمُ
ٱلْإِيمَٰنَ وَأَيَّدَهُم بِرُوحٍ مِّنْهُ ۖ وَيُدْخِلُهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى
مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَا ۚ رَضِىَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُواْ
عَنْهُ ۚ أُوْلَٰٓئِكَ حِزْبُ ٱللَّهِ ۚ أَلَآ إِنَّ حِزْبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ٢٢ ﴾ المجادلة : ٢٢

3. አል–ሙዘሚል(73):15
4. አል–ጂን(72):18

«በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች፥ አላህና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፤ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፤ ከርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል፤ ከሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጧቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ ያገባቸዋል፤ አላህ ከነርሱ ወዷል። ከርሱም ወደዋል፤ እነዚያ የአላህ ሕዝቦች ናቸው፤ ንቁ የአላህ ሕዝቦች እነሱ ምቾታቸውን የሚያገኙ ናቸው።»[5]

የእብራሂም ሃይማኖት የሆነው ሐኒፍይ—ያ (ወደ እውነት ማዘንበል) —አላህ ለትዕዛዙ ቅን ተገዥ እንድትሆን ይምራህና— አንድ አላህ ብቻ ሃይማኖትን ለርሱ ፍጹም በማድረግ መገዛት ወይም ማምለክ መሆኑን ዕወቅ፤ ሰዎች በሙላ ይህንኑ እንዲያደርጉ አላህ አዟል። ሰውን የፈጠረው ለዚህ ዓላማ መሆኑንም እንደሚከተለው ገልጿል:-

﴿وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴾

«ጋኔንንና ሰውንም ፣ ሊገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።»[6]

ሊገዙኝ ማለት እኔን ብቻ ሊያመልኩኝ ማለት ነው። ከአላህ ትዕዛዝ ሁሉ ትልቁና ዋነኛው ተውሒድ ነው። ተውሒድ ማለትም አንድ አላህን ብቻ መገዛት እርሱን ብቻ ማምለክ ማለት ነው። አላህ ከከለከላቸውና ካገዳቸው ነገሮች ሁሉ ከባዱና ዋነኛው ደግሞ ሽርክ ሲሆን እሱም ከአላህ ጋር ሌላ ፍጡር በማጋራት ባዕድ አምልኮ መፈጸም ነው። ለዚህ ማስረጃው ቀጥሎ የተመለከተው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:- ﴿وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا﴾.

---

5. አል—ሙጃደላህ(58):22
6. አል—ዛሪያት(51):56

«አላህንም ተገዙ! በርሱም ምንንም አታጋሩ።..»[7]

አንድ ሰው ሊያውቃቸው የሚገቡ ሶስት መሰረታዊ መርሆዎች ምንድ ናቸው? ተብለህ ብትጠየቅ:- ፈጣሪ ጌታን፣ የርሱን ሃይማኖትና ነቢዩ ሙሐመድን(ሰዐወ) ማወቅ ነው ብለህ መልስ።

## አንደኛው መሠረታዊ መርህ

ጌታህ ማነው? ከተባልክ፣ ጌታየ በችሮታውና በጸጋው እኔንና ዓላማትን በመላ ያስገኘውና ያሳደገው አላህ ነው። እርሱ የማመልከው የምገዛለት አምላኬ ሲሆን ከርሱ በስተቀር ሌላ የማመልከው ጌታ የለኝም በል። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَـٰلَمِينَ ﴾

«ምስጋና ለአላህ ይገባው ! የአለማት ጌት ለኾነው!»[8]

ከአላህ በስተቀር ያለው ነገር ሁሉ ፍጥረት ሲሆን እኔም የዚሁ ፍጥረት አንዱ አካል የሆንኩ ፍጡር ነኝ።

ጌታህን በምን አወቅህ? ተብለህ ከተጠየክ:- በምልክቶቹና በፍጥረታቱ አማካይነት ነው በል። ሌሊትና ቀን፣ ጸሐይና ጠረቃ ከምልክቶቹ አንዱ ሲሆን ሰባቱ ሰማያትና ሰባቱ ምድር፣

7. አል-ኒሳእ(4):36
8. አል-ፋቲሐ(1):2

በውስጣቸውና በመካከላቸው ያሉት ሁሉ የፍጥረታቱ አካል ናቸው። ለዚህ ማስረጃ የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَمِنْ ءَايَـٰتِهِ ٱلَّيْلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ ۚ لَا تَسْجُدُوا لِلشَّمْسِ وَلَا لِلْقَمَرِ وَٱسْجُدُوا لِلَّهِ ٱلَّذِى خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمْ إِيَّاهُ تَعْبُدُونَ ﴾ سورة فصلت: ٣٧.

﴿ إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ يَطْلُبُهُۥ حَثِيثًا(١) وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتٍۭ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَـٰلَمِينَ ﴾ سورة الأعراف: ٥٤

«ሌሊትና ቀንም፣ ፀሐይና ጨረቃም፣ ከምልክቶቹ ናቸው፤ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፤ ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፤ እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደ ኾናችሁ(ለሌላ) አትስገዱ።»[9]

«ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፤ ከዚያም በዐርሹ ላይ ተደላደለ፤ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል፤ ፀሐይና ጨረቃንም፣ ከዋክብትንም በትዕዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው) ፤ ንቁ ፤ መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው፤ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ።»[10]

-ጌታ ማለት የሚግገዙትና የሚያመልኩት ፈጣሪ አምላክ ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱعْبُدُوا رَبَّكُمُ ٱلَّذِى خَلَقَكُمْ وَٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿٢١﴾ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلْأَرْضَ فِرَٰشًا(٢) وَٱلسَّمَآءَ بِنَآءً وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزْقًا لَّكُمْ ۖ فَلَا تَجْعَلُوا لِلَّهِ أَندَادًا(١) وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴾ سورة البقرة: ٢٣

9. ሓ.ሚም. አል-ሰጅደህ(41):37
10.አል-አዕራፍ(7):54

«እላንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን፣ እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን(የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጅላልና።(እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ፣ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም፣ (ከደመና) ውሃን ያወረደ፣ በርሱም ከፍሬዎቹ ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው፤ እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ፣ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ።»[11]

እብኑ ከሲር(ረዐ) የተባሉ የቁርአን ተንታኝ የላይኛውን አንቀጽ አስመልክተው ሲናገሩ «እዚህ የተዘረዘሩትን ነገሮች የፈጠረ ፈጣሪ ለአምልኮት(ለዕባዳ) ብቸኛው ባለመብት ነው» ብለዋል።

እንደ መታዘዝ (እስላም) ፣ እምነት (ኢማን) ፣ ደግነት(እሕሳን)፣ ጸሎትና ምልጃ (ዱዓእ) ፣ ፍርሃት ወይም ስጋት (ኸውፍ) ፣ ተስፋና እምነት መጣል (ረጃእ)፣ መመካት (ተወኩል)፣ ተስፋን በመጠበቅ መታዘዝ (ረግባህ) ፣ ቅጣትን በመፍራት መታዘዝ (ረህባ)፣ ራስን ዝቅ አድርጎ በፍጹምነት መግገዛት(ኩሹዕ)፣ መፍራት (ከሽየህ)፣ ከስህተት ተመልሰው በመጸጸት ምህረት መጠየቅ (እናበህ)፣ ረደኤት (እስትዓነህ)፣ ጥበቃ (እስትዓዘህ) እና እገዛን መለመን(እስትጋሰህ)፣ እርድ ማቅረብ፣ መሳል(ነዝር) እና የመሳሰሉት አላህ ያዘዛቸው የዕባዳ ዓይነቶች ሁሉ ለአላህ ብቻ እንጂ ለማንም አይገቡም። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ وَأَنَّ ٱلْمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا۟ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدًا ﴾ سورة الجن: ١٨.

«እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው፤ (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ፣ (ማለትም)።»[12]

---

10. አል-አዕራፍ(7):54
11. አል-በቀራህ (2):22
12. አል-ጂን(72):18

ከነዚህ የዕባዳ ዓይነቶች አንዱንም ከአላህ አሳልፎ ለሌላ ወገን ያዋለ ሰው በአላህ ያጋራ ሙሽሪክ ከሓዲ(ካፊር) ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ وَمَن يَدْعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَـٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرْهَـٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلْكَـٰفِرُونَ ﴾

«ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ፣ ለርሱ በርሱ ማስረጃ የሌላውን የሚገዛ ሰው፣ ምርመራው እጌታው ዘንድ ብቻ ነው፤ እነሆ ከሓዲዎች አይድኑም።»[13]

በነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን:-

«الدعاء مخ العبادة»

«ጸሎት(ዱዓእ) የአምልኮት(የዕባዳ) አስኳል ነው»[14]

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው :-

﴿ وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدْعُونِىٓ أَسْتَجِبْ لَكُمْ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِى سَيَدْخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ ﴾ سورة غافر: ٦٠ .

«ጌታችሁም አለ:- ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁ፤ እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።»[15]

13. አል–ሙእሚኑን(23)·117
14. ቲርሚዚ የዘገቡት ሐዲስ
15. አል–ሙእሚን(40)·60

ፍጹም በሆነ ሁኔታ ሊፈሩት የሚገባ አላህ ብቻ ለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ فَلَا تَخَافُوهُمْ وَخَافُونِ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴾ سورة آل عمران : ١٧٥

«..አትፍሩዋቸውም፤ ምእምናንም እንደኾናችሁ ፍሩኝ።»[16]

ተስፋ የሚጣለው (ረጃእ) በአላህ ላይ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ فَمَن كَانَ يَرْجُوا لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا ﴾
سورة الكهف : ١١٠

«.. የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ በጌታውም መግገዛት አንድንም አያጋራ፤ በላቸው።»[17]

መመካት (ተወኩል) በአላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተሉት የአላህ(ሱወ) አንቀጾች ናቸው:-

﴿ وَعَلَى اللَّهِ فَتَوَكَّلُوا إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴾ سورة المائدة : ٢٣

﴿ وَمَن يَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ فَهُوَ حَسْبُهُ ﴾ سورة الطلاق : ٣

«..ምእምናንም እንደኾናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ..»[18]

«..በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው፤ እርሱ በቂው ነው።»[19]

---

16. አሊ ዒምራን(3):175
17. አል-ከሀፍ(18):110
18. አል-ማኢዳህ(5):23
19. አል-ጦላቅ(65):3

መከጀል (ረግበህ)፣ መፍራት(ረህበህ)እና በተዋራጅነት መታዘዝን (ኹሹዕ) ለአላህ ብቻ መፈጸም የሚገባ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿إِنَّهُمْ كَانُوا يُسَارِعُونَ فِي الْخَيْرَاتِ وَيَدْعُونَنَا رَغَبًا وَرَهَبًا وَكَانُوا لَنَا خَاشِعِينَ ﴿٩٠﴾﴾ سورة الانبياء: ٩٠

«..ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም፤ ነበሩ ለኛ ተዋራጆችም ነበሩ፤ ።»[20]

ሊፈሩትና ሊጠነቀቁት የሚገባ አላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ فَلَا تَخْشَوْهُمْ وَاخْشَوْنِي ﴾ الآية. سورة البقرة: ١٥٠

«..አትፍሩዋቸውም፤ ፍሩኝም፤ ..»[21]

በሠሩት ኃጢአት ተጸጽተው ምህረት በመለመን መማለስ (እናበህ) የሚገባው ወደ አላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው ቀጥሎ የተመለከተው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَأَنِيبُوا إِلَىٰ رَبِّكُمْ وَأَسْلِمُوا لَهُ ﴾ الآية سورة الزمر: ٥٤

«..ወደ ጌታችሁ(በመጸጸት) ተመለሱ፤ ለርሱም ታዘዙ።»[22]

እርዳታ መለመን(እስትዓነህ) የሚገባው ከአላህ ስለመሆኑ ማስረጃው ቀጥሎ የሰፈረው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ ﴾ من سورة الفاتحة: ٥

---

20. አል-አንቢያ(21):90
21. አል-በቀራህ(2):150
22. አል-ዙመር(39):54
23. አል-ፋቲሐህ(1):5

«አንተን ብቻ እንገገዛለን፤ አንተንም ብቻ ርዳታ እንለምናለን።» [23]

ረደኤት መጠየቅን አስመልክቶ በነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን:-

اذا استعنت فاستعن بالله .

«(በሚያጋጥምህ ችግር ላይ) እገዛ ስትፈልግ በአላህ ታገዝ።» [24]

ጥበቃ መለመን የሚገባው ከአላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ۝١ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ﴾

«በል:- በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ። የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በኾነው፤ » [25]

ረድኤት ለማግኘት ልመና መቅረብ የሚገባው ለአላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ إِذْ تَسْتَغِيثُونَ رَبَّكُمْ فَٱسْتَجَابَ لَكُمْ ﴾ الآية سورة الأنفال : ٩

«ከጌታችሁ ርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ፤ .. ለናንተ የተቀበላችሁን፥ (አስታውሱ)።» [26]

---

24. ቲርሚዚ የዘገቡት ሐዲስ
25. አል-ናስ (114):1-2
26. አል-አንፋል (8):9

እርድን ለአምልኮት ማቅረብ የሚገባው ለአላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ ﴿١٦٢﴾ لَا شَرِيكَ لَهُ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ ﴾ سورة الأنعام: ٦٢

«ስግደቴ መገገዛቴም ሕይወቴም፣ ሞቴም፣ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል። ለርሱ ተጋሪ የለውም፤ በዚህም (በማተራት) ታዘዝኩ፤ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ(በል)።»[27]

እንስሳትን ለአምልኮት ብሎ ማረድን (መሰዋትን) አስመልክቶ ሐዲስ ውስጥ የሚከተለው ተመልክቷል:-

«لعن الله من ذبح لغير الله»

«ለአምልኮት ብሎ ለአላህ ሳይሆን ለሌሎች አማልክት እንስሳ ያረደ(የሰዋ) ማንኛውንም ሰው አላህ ረግሞታል።»[28]

ስዕለት (ነዝር) መሳል የሚገባው ለአላህ ብቻ ስለመሆኑ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ يُوفُونَ بِالنَّذْرِ وَيَخَافُونَ يَوْمًا كَانَ شَرُّهُ مُسْتَطِيرًا ﴾ سورة الدهر: ٧

«(ዛሬ) በስለታቸው ይሞላሉ፤ መከራው ተሰራጪ የኾነንም ቀን ይፈራሉ።»[29]

---

27. አል-አንዓም(6):162-163
28. ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ
29. አል-ደህር(76):7

## ሁለተኛው መሰረታዊ መርሕ

ሁለተኛው መሰረታዊ መርህ የእስላምን ሃይማኖት በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ ማወቅ ነው። ይህም የአላህን ተውሒድ በማረጋገጥ ለርሱ መገዛት፣ በታዛዥነት ለርሱ ተመሪ መሆንና ከሽርክ መጥራት ነው። የኢስላም ሃይማኖት ሶስት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነሱም የኢስላም (የታዛዥነት)፣ የኢ.ማን (የአማኝነት) እና የኢሕሳን (የፍጹም ተገዥነት) ደረጃዎች ናቸው። እያንዳንዱ ደረጃም የራሱ የሆኑ ማዕዘናት (አርካን) ያሉት ሲሆን የእስላም ማዕዘናት አምስት ናቸው። እነሱም:- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቆና አዘውትሮ መስገድ፣ ዘካትን መክፈል፣ የረመዷንን ወር መጾምና ሐጅ ማድረግ ናቸው። የመጀመሪያው ማዕዘን የሸሃዳ ማስረጃ የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ شَهِدَ ٱللَّهُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ وَأُو۟لُوا۟ ٱلْعِلْمِ قَآئِمًۢا بِٱلْقِسْطِ
لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴾ سورة آل عمران: ١٨

«አላህ፣ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲሆን፣ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ፤ መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)፤ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊው ጥበበኛው ነው።» [30]

ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ማለት ከአንድ አላህ በስተቀር ሊገዙትና ሊያመልኩት የሚገባ እውነተኛ አምላክ የለም ማለት ነው። «ላ እላሀ» የሚለው ሐረግ ከአላህ ሌላ የሚመለኩ

---

30. አል-ዒምራን(3):18

አማልክትን በሙሉ የሚያስተባብል ነው። «አል-ላል-ኋሀ» የሚለው ሐረግ ደግሞ ያለ ምንም አጋርና ሸሪክ አምላክነትን ለአንድ አላህ ብቻ የሚያረጋግጥ በጌትነቱና በንግሥናው ምንም ሸሪክ እንደሌለው ሁሉ በአምልኮት (በዕባዳም) ሸሪክ የሌለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህን ጽንሰ-ሐሳብ የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ያብራራል:-

﴿ وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ وَقَوْمِهِۦٓ إِنَّنِى بَرَآءٌ مِّمَّا تَعْبُدُونَ ﴿٢٦﴾ إِلَّا ٱلَّذِى
فَطَرَنِى فَإِنَّهُۥ سَيَهْدِينِ ﴿٢٧﴾ وَجَعَلَهَا كَلِمَةًۢ بَاقِيَةً فِى عَقِبِهِۦ لَعَلَّهُمْ
يَرْجِعُونَ ﴿٢٨﴾ ﴾ سورة الزخرف: ٢٦ - ٢٨،

﴿ قُلْ يَٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ تَعَالَوْا۟ إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَآءٍۭ بَيْنَنَا
وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا ٱللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِۦ شَيْـًٔا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا
بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ ٱللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا۟ فَقُولُوا۟ ٱشْهَدُوا۟ بِأَنَّا
مُسْلِمُونَ ﴿٦٤﴾ ﴾ سورة آل عمران: ٦٤،

«የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በኛና በናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፤ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፥ በርሱም ምንንም ላናጋራ፤ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እምቢ ቢሉም:- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው።» [32]

31. አል-ዙኽሩፍ(43):26-28
32. አሊ-ዒምራን(3):64

ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን ለመመስከር ማስረጃው ቀጥሉ የተመለከተው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴾ سورة التوبة : ١٢٨

«ከነሳችሁ የኾነ፣ ችግራችሁ በርሱ ላይ ጥኑ የኾነ፣ በናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእምናን ርህሩህ አዛኝ የኾነ መልክተኛ፣ በእርግጥ መጣላችሁ።»[33]

ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር ማለት ያዘዙትን መፈጸም፣ የተናገሩትን እውነት ነው ብሎ መቀበል፣ የከለከሉትንና ያስጠነቀቁትን ነገር መራቅና አላህ ራሱ በደነገገው ሕግ መሰረት ብቻ የሚመለክ(ዕባዳ የሚደረገለት) መሆን ይገባል ማለት ነው።

የሶላትና የዘካት ማስረጃና የተውሒድ ትርጉም የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ وَمَآ أُمِرُوٓا۟ إِلَّا لِيَعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤْتُوا۟ ٱلزَّكَوٰةَ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلْقَيِّمَةِ ۝٥ ﴾

سورة البينة : ٥

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ۝١٨٣ ﴾ سورة البقرة : ١٨٣

33. አል–ተውባህ(9):128

«አላህን፣ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊገገዙት፣ ሶላትንም እስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)። ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።»[34]

«እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ፣ በናንተም ላይ ተጻፈ፣ (ተደነገገ)፣ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።»[35]

የሐጅ ማስረጃ ደግሞ የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا ۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ اللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ الْعَالَمِينَ ﴾ سورة آل عمران : ٩٧

«.. ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፤ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።» [36]

## ሁለተኛው ደረጃ

ሁለተኛው ደረጃ ወይም እርከን ደግሞ ኢማን (እምነት) ሲሆን እሱም ከሰባ ሶስት እስከ ሰባ ዘጠኝ ያህል ቅርንጫፎች አሉት። ከፍተኛው ቅርንጫፍ «ላእላህ እል—ላል—ሏህ» የሚለው ቃለ ተውሒድ ሲሆን ዝቅተኛው ከመንገድ ላይ እንቅፋት ማስወገድ(ማንሳት) ነው። የማፈር ስሜት(ሐያእ) እንኳ የእምነት አንዱ ቅርንጫፍ ነው።»[37] የኢማን ማዕዘናት ስድስት ናቸው። እነሱም በአላህ ፣ በመላእኮቹ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ ፣

34. አል—በይናህ(98):5
35. አል—በቀራህ(2):183
36. አሊ-ዒምራን(3):97
37. ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

በመጨረሻው ቀን፣ በቀደር ማለትም መልካሙም ሆነ መጥፎው ነገር ሁሉ በአላህ መሻትና በርሱ ውሳኔ ብቻ የሚከሰት መሆኑን ማመን ናቸው። ለነዚህ ስድስት ማዕዘናት ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ لَّيْسَ الْبِرَّ أَن تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَٰكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ ﴾ سورة البقرة: ١٧٧،

«መልካም ሥራ፣ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም! ግን መልካም ሥራ፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም ያመነ ሰው፣..»[38]

በቀደር ስለማመን ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿ إِنَّا كُلَّ شَيْءٍ خَلَقْنَاهُ بِقَدَرٍ ﴿٤٩﴾ ﴾ سورة القمر: ٤٩

«እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው።»[39]

## ሦስተኛ ደረጃ

ሦስተኛ ደረጃ እሕሳን(ፍጹማዊ ተገዥነትና ደግነት) ሲሆን እሱም አንድ ማዕዘን ብቻ ነው ያለው። ማዕዘኑም ልክ እንደምታየው ሆነህ አላህን ማምለክ ነው። አንተ ባታየውም እርሱ ያየሃልና። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

38. አል–በቀራህ(2):177

39. አል–ቀመር(54):49

«አላህ ከነዚያ ከሚፈሩትና ከነዚያም እነሱ መልካም ሰሪዎች ከሆኑት ጋር ነውና።»[40]

«አሸናፊ አዛኝ በሆነው (ጌታህ) ላይም ተጠጋ። በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ፣ በሚያይህ፣ ከሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም፣ (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)፣ እነሆ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና።»[41]

«(ሙሐመድ ሆይ!) በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፣ ከርሱም ከቁርአን አታነብም፣ ማንኛውንም ሥራ (አንተም ሰዎቹም) አትሰሩም፣ በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ብንኾን እንጂ! .. »[42]

ለዚህ ለእሕሳን ማስረጃ ከሱን—ና ለመጥቀስ ከዑመር ብን አልኸጧብ(ረዐ) የተዘገበውና በስፋት የታወቀው የሚከተለው የጅብሪል ሐዲስ ነው፡-

وبينما نحن جلوس
عند النبي ﷺ إذ طلع علينا رجلٌ شديد بياض
الثياب شديد سواد الشعر لا يرى عليه أثر السفر(٣) ولا
يعرفه منا أحد فجلس إلى النبي ﷺ فأسند ركبتيه إلى
ركبتيه ووضع كفيه على فخذيه وقال: يامحمد أخبرني
عن الإسلام فقال: أن تشهد أن لا إله إلا الله وأن
محمداً ﷺ رسول الله ، وتقيم الصلاة وتؤتي
الزكاة وتصوم رمضان ، وتحج البيت إن استطعت
إليه سبيلاً قال: صدقت، فعجبنا له يسأله
ويصدقه ، قال أخبرني عن الايمان، قال: أن تؤمن

40. አል-ነሕል(16):128
41. አል-ሹዐራእ(26):217-220
42. ዩኑስ (10):61

بالله وملائكته وكتبه ورسله واليوم الآخر وبالقدر خيره وشره قال: أخبرني عن: الاحسان: قال: أن تعبد الله كأنك تراه فإن لم تكن تراه فأنه يراك، قال أخبرني عن الساعة؟ قال: ما المسؤول عنها بأعلم من السائل؟ قال: أخبرني عن أماراتها قال: أن تلد الأمة ربتها، وأن ترى الحفاة العراة العالة رعاء الشاة يتطاولون في البنيان. قال: فمضى، فلبثنا مليا فقال: ياعمر؛ أتدرون من السائل؟ قلنا الله ورسوله أعلم، قال هذا جبريل أتاكم يعلمكم أمر دينكم»

ከዕለታት አንድ ቀን የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ዘንድ ተቀምጠን እያለን አንድ ልብሱ በጣም ነጭ የሆነ ፀጉሩ በጣም የጠቆረ የጉዞ ምልክት የማይታይበትና ከመካከላችን አንድም ሰው የማያውቀው ሰው ከተፍ አለና መጥቶ ጉልበቶቹን ከነቢዩ(ሰዐወ) ጉልበቶች አስደገፎ መዳፎቹን ታፋው ላይ አሳርፎ ተቀመጠ። ከዚያም « ሙሐመድ ሆይ! ስለ እስላም ንገረኝ » አለ። የአላህ መልክተኛም (ሰዐወ) እንዲህ አሉት:- « እስላም ማለት ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ መሆኑን መመስከር፣ ሰላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፣ ዘካትን (የግዴታ ምጽዋትን) መክፈል፣ የረመዷንን ወር መጾምና አቅም ካላና ከተቻለ ሐጅ ማድረግ (ወደ መካ ተጉዞ በደንቡ መሰረት ሥርዓተ ጸሎት ማድረስ) ነው።» ትክክለኛ ነህ አላቸው(ጠያቂው)። ከዚያም ስለ እምነት (ኢማን) ንገረኝ አለ። (ነቢዩም) እንዲህ አሉት:- «በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው(የፍርድ) ቀን ማመንና መልካሙም ሆነ መጥፎው በአላህ ዕውቀትና በውሳኔው ብቻ የሚከሰት መሆኑን (በቀደር) ማመን ነው።» ትክክለኛ ነህ አለ። ስለ ቱሩፋት (እሕሳን) ንገረኝ አለ። (ነቢዩም) እንዲህ አሉት:- «አንተ ባታየውም እርሱ ያያሃልና ልክ እንደምታየው ሆነህ አላህን መገዛት ነው»

ስለ ዓለም ፍጻሜ (ትንሳኤ መች እንደሆን) ንገረኝ አላቸው። «በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ የሚያውቀው ነገር የለም።» አሉት።

(ጠያቂው) ሂዶ ትንሽ ከቆየን በኋላ «ዑመር ሆይ! ጠያቂው ማን እንደሆነ ታቃላችሁን?» በማለት ነቢዩ ጠየቁ። «አላህና መልክተኛው ናቸው የሚያውቁት» አልናቸው።

«እርሱ ጅብሪል ነው ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ነው የመጣው» አሉ። ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

## ሦስተኛው መሰረታዊ መርሕ

ሦስተኛው መሰረታዊ መርሕ ነቢያችሁን ሙሐመድን (ሰዐወ) ማወቅ ሲሆን እርሳቸውም ሙሐመድ ብን ዐብደሏህ ብን ዐብዱል ሙጥ–ጠሊብ ብን ሃሺም ናቸው። ሃሺም የቁረይሽ ጎሳ ነገድ ነው። ቁረይሽ የዐረብ ነገድ ሲሆን ዐረቦች ደግሞ የአላህ ወዳጅ(ኸሊል) ኢብራሂም ልጅ የኢስማዒል (ሰዐወ) ልጆች ናቸው። በዚህ ዓለም ላይ የኖሩት ለ63 ዓመት ሲሆን 40 ዓመት በነቢይነት ከመላካቸው በፊት ነው። ሃያ ሶስቱን ዓመት መልክተኛ ነቢይ በመሆን ነበር ያሳለፉት። ነቢይ የሆኑት « اقرأ » ወይም «አንብብ» የሚለው የአላህ ቃል በተላለፈላቸው ጊዜ ሲሆን መልክተኛ (ረሱ–ል) የሆኑት ደግሞ በሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል መሰረት ነው፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلْمُدَّثِّرُ ۝١ قُمْ فَأَنذِرْ ۝٢ وَرَبَّكَ فَكَبِّرْ ۝٣ وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ ۝٤ وَٱلرُّجْزَ فَٱهْجُرْ ۝٥ وَلَا تَمْنُن تَسْتَكْثِرُ ۝٦ وَلِرَبِّكَ فَٱصْبِرْ ﴾ المدثر: ١-٧

«አንተ(ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ተነሳ! አስጠንቅቅም። ጌታህንም አክብር። ልብስህንም አጥራ። ጣዖትንም ራቅ። ማብዛትንም የምትፈልግ ኾነህ! (በረከትን) አትለግስ! (ጥቂት ሰጥተህ ብዙ እንዲሰጡህ አታድርግ)።»[43]

43. አል–ሙደሢር(74):1–7

«ተነሳ አስጠንቅቅም» ማለት ሰዎች በአላህ እንዳያሻርኩ አስጠንቅቃቸው፣ አንድ አላህን ብቻ እንዲገገዙ ወደ ተውሒድ ጥሪ አድርግላቸው ማለት ነው። «ጌታህንም አክብር» ማለት እርሱን ብቻ በመገገዛት በተውሒድ አክብረው ማለት ነው። «ልብስህንም አጥራ» ማለት ቃልና ተግባርህን ከሽርክ ርክሰት አጽዳ ማለት ነው። «ጣዖትንም ራቅ» ማለት ደግሞ ጣዖታትን ሁሉ ከጣዖታውያኑ ጭምር ከነአካቴው እርግፍ አድርጎ መተውና ከጣዖታቱና ከተከታዮቻቸው እስከመጨረሻው መላቀቅ ማለት ነው። ነቢዩ(ሰዐወ) ይህንኑ ተግባር በማከናወንና ለተውሒድ ጥሪ በማድረግ አሥሩን ዓመታት አሳለፉ። ከአሥር ዓመት በኋላ ወደ ሰማያት አሳረጋቸውና አምስቱ ዕለታዊ ሶላቶች በግዴታነት ተደነገጉ። ለሶስት ዓመት መካ ውስጥ ሶላቱን እየፈጸሙ ከቆዩ በኋላ ወደ መዲና ለመሰደድ(ለህጅራ) ታዘዙ። ህጅራ ወይም ስደት ማለት የሽርክን አገር ለቆ ወደ እስላም አገር መዛወር ማለት ነው። ሽርክ ከተንሰራፋበት አገር ወደ እስላም አገር መሰደድ(ህጅራ) በዚህ ሕዝበ እስላም(ኡም—መህ) ላይ ግዴታው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚጸና ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَوَفَّىٰهُمُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ
ظَالِمِىٓ أَنفُسِهِمْ قَالُوا۟ فِيمَ كُنتُمْ قَالُوا۟ كُنَّا مُسْتَضْعَفِينَ فِى ٱلْأَرْضِ
قَالُوٓا۟ أَلَمْ تَكُنْ أَرْضُ ٱللَّهِ وَٰسِعَةً فَتُهَاجِرُوا۟ فِيهَا فَأُو۟لَٰٓئِكَ مَأْوَىٰهُمْ
جَهَنَّمُ وَسَآءَتْ مَصِيرًا ﴿٩٧﴾ إِلَّا ٱلْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ ٱلرِّجَالِ
وَٱلنِّسَآءِ وَٱلْوِلْدَٰنِ لَا يَسْتَطِيعُونَ حِيلَةً وَلَا يَهْتَدُونَ سَبِيلًا ﴿٩٨﴾
فَأُو۟لَٰٓئِكَ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَعْفُوَ عَنْهُمْ وَكَانَ ٱللَّهُ عَفُوًّا غَفُورًا ﴾

سورة النساء: ٩٩.

«እነዚያ (ለእምነት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ሆነው መላእክት (በድር) የገደሉዋቸው ፣ (መላእክት ለነርሱ) በምን ነገር ላይ ነበራችሁ? አሏቸው፤ በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን አሉ፤ የአላህ ምድር ትሰደዱበት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን? አሉዋቸው፤ እነዚህም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፤ በመመለሻነትም ከፋች!፤ ግን ከወንዶችና ከሴቶች ከሕፃናትም ሲኾኑ (ለመውጣት) መላን የማይችሉና መንገድንም የማይመሩ(የማያውቁ) ደካሞች (ቅጣት የለባቸውም)፤ እነዚያም አላህ ከነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል፤ አላህም ይቅር ባይ መሓሪ ነው።»[44]

﴿ يَـٰعِبَادِىَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّ أَرْضِى وَٰسِعَةٌ فَإِيَّـٰىَ فَٱعْبُدُونِ ﴾ العنكبوت : ٥٦ .

«እላንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ምድሬ በእርግጥ ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱ)፤ እኔንም ብቻ ተገዙኝ።»[45]

ይህ አንቀጽ መሰደድን ትተው መካ ውስጥ የቀሩትን ሙስሊሞች አስመልክቶ የተላለፈ ነው በማለት አል–ቡኻሪ ተናግረዋል። የስደትን አስፈላጊነት በተመለከተ የሱን–ና ማስረጃ የሚከተለው የነቢዩ (ሰዐወ) ሐዲስ ነው:-

«لا تنقطع الهجرة حتى تنقطع التوبة ولا تنقطع التوبة حتى تطلع الشمس من مغربها»

44. አል–ኒሳእ(4):97–99
45. አል–ዐንከቡት(29):56

«ተውባህ (ንስሐ) እስኪቋረጥ ድረስ ሀጅራ አይቋረጥም፣ ተውባህ ደግሞ ፀሐይ በምዕራብ በኩል ተመልሳ እስካልወጣች ድረስ አይቋረጥም።»

ነቢዩ (ሰዐወ) መዲና ውስጥ ረግተው በተቀመጡ ጊዜ እንደ ዘካት፣ ጾም ፣ሐጅ፣ አዛን፣ ጅሃድ፣ ለበጎ ተግባር ማዘዝና ከክፉው መከልከል ወዘተ ያሉ ሌሎች የእስላም ድንጋጌዎችን እንዲያስፈጽሙ ታዘዙ። ይህንን ሲያደርጉ አሥር ዓመታት ካሳለፉ በኋላም ዐረፉ። ሃይማኖታቸው ግን ለዘለዓለም ቀሪ ሆና ቀጠለ። ነቢዩ (ሰዐወ) መልካም የሆነውን ነገር ለሕዝባቸው ሳያመላክቱ መጥፎ ከሆነውም ነገር ሳያስጠነቅቁ የተውት አንድም ነገር የለም። ለሕዝባቸው ያመላከቱት መልካም ነገር ተውሒድና አላህ የሚቀበላቸውና የሚወዳቸው ነገሮች ሁሉ ሲሆን ያስጠንቀቁት መጥፎ ነገሮች ደግሞ ሽርክና አላህ የሚጠላቸውና የማይቀበላቸውን ነገሮች ሁሉ ነው። አላህ(ሱወ) ወደ መላው የሰው ልጅ የላካቸው ሲሆን ትዕዛዛቸውን የመፈጸም ግዴታ በሁለቱም በሰው ልጆችና በጂኖች ላይ ጥሏል።

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ قُلْ يَاأَيُّهَا النَّاسُ إِنِّي رَسُولُ اللَّهِ

إِلَيْكُمْ جَمِيعًا ﴾ سورة الأعراف: ١٥٨

«(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው:- እላንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፣ ..»[46]

---

46.አል-አዕራፍ (7):158

«በርሳቸው ነቢይነትም አላህ(ሱወ) ሃይማኖትን ሙሉእ አድርጓል። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗاۚ﴾ سورة المائدة: ٣.

«..ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ! ..»[47]

ነቢዩ(ሰሀወ) ስለመሞታቸው ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿إِنَّكَ مَيِّتٞ وَإِنَّهُم مَّيِّتُونَ ۝٣٠ ثُمَّ إِنَّكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ عِندَ رَبِّكُمۡ تَخۡتَصِمُونَ﴾ سورة الزمر: ٣٠.

«አንተ ሟች ነህ፣ እነርሱም ሟቾች ናቸው። ከዚያም እናንተ በትንሳኤ ቀን እጌታችሁ ዘንድ ትከራከራላችሁ።»[48]

ሰዎች ከሞቱ በኋላ በትንሳኤ ቀን ዳግም ይቀሰቀሳሉ። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿مِنۡهَا خَلَقۡنَٰكُمۡ وَفِيهَا نُعِيدُكُمۡ وَمِنۡهَا نُخۡرِجُكُمۡ تَارَةً أُخۡرَىٰ﴾

﴿وَٱللَّهُ أَنۢبَتَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ نَبَاتٗا ۝١٧ ثُمَّ يُعِيدُكُمۡ فِيهَا وَيُخۡرِجُكُمۡ إِخۡرَاجٗا﴾ سورة نوح: ١٧

47. አል-ማኢዳህ(5):3
48. አል-ዙመር(39):30

«ከርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ፤ በርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን፤ ከርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን።»[49]

«አላህም ከምድር ማብቀልን አበቀላችሁ። ከዚያም በውስጧ ይመልሳችኋል። ማውጣትንም ያወጣችኋል።»[50]

ሰዎች ከሞት ተቀስቅሰው ከተነሱ በኋላም በመጀመሪያው ሕይወታቸው ስለፈጸሟቸው ነገሮች ሁሉ ተመርምረው እንደየሥራቸው ዋጋ ያገኛሉ። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:- ﴿ وَلِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ لِيَجْزِيَ الَّذِينَ أَسَاءُوا بِمَا عَمِلُوا وَيَجْزِيَ الَّذِينَ أَحْسَنُوا بِالْحُسْنَى ﴾ سورة النجم: ٣١

«በሰማያት ያለውና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው። እነዚያ ያጠፉትን በሰሩት ሊቀጣ፤ ያሳመሩትንም በመልካሚቱ(ገነት) ሊመነዳ (የጠመመውንና የቀናውን ያውቃል)።»[51]

ከሞት በኋላ እንደገና መቀስቀስ መኖሩን ያስተባበለ ሰው ከሐዲ ወይም ካፊር ይሆናል። ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ زَعَمَ الَّذِينَ كَفَرُوا أَن لَّن يُبْعَثُوا قُلْ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبْعَثُنَّ
ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلْتُمْ وَذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ ﴿٧﴾ ﴾

49. ጣሃ(20)፡55
50. ኑሕ(71)፡17
51. አል–ነጅም(53)፡31

«እነዚያ የካዱት በፍጹም የማይቀሰቀሱ መኾናቸውን አሰቡ፤ አይደለም በጌታዬ እምላለሁ፤ በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ ፤ ከዚያም በሰራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ፤ ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው በላቸው።»[52]

አላህ (ሱ.ወ) መልክተኞችን ሁሉ አብሳሪዎች አስፈራሪዎች (አስጠንቃቂዎች ) አድርጎ ልኳል። ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿ رُسُلًا مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةٌۢ بَعْدَ ٱلرُّسُلِ ﴾ سورة النساء: ١٦٥

«ከመልክተኞች በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር፤ አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች(ላክን)፤..»[53]

የመጀመሪያው መልክተኛ ነቢዩ ኑሕ ሲሆኑ የመጨረሻውና የነቢዮች መደምደሚያ የሆኑት መሐመድ(ሰዐወ) ናቸው። ነቢዩ ኑሕ የመጀመሪያው መልክተኛ(ረሱ—ል) ስለመሆናቸው ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿ إِنَّآ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ كَمَآ أَوْحَيْنَآ إِلَىٰ نُوحٍ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعْدِهِۦ ﴾ النساء: ١٦٣

«እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደነበሩት ነቢያት እንዳወረድን፤ ወደ አንተም አወረድን፤ ..»[54]

52. አል—ተጋቡን(64):7
53. አል—ኒሳእ(4):165
54. አል—ኒሳእ(4):163

አላህ (ሱ.ወ) ከኑሕ ጀምሮ እስከ ሙሐመድ ድረስ ያሉትን መልክተኞች የላከባቸውን ሕዝቦች ሁሉ እርሱን ብቻ እንዲገዙ በማዘዝ ጣዖታትን እንዳያመልኩ በጥብቅ ከልክሏቸዋል። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَسُولًا أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوتَ ﴾ سورة النحل: ٣٦

«በሕዝቦች ሁሉ ውስጥ፤ አላህን ተገዙ፤ ጣዖታትንም ራቁ፤ በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፤ ..»[55]

ጣዖታትን በማስተባበል በአላህ ብቻ ማመን በሁሉም ሰው ላይ የተደነገገ ግዴታ ነው። ኢብኑል ቀይም(ረሐ) ጣዖት ማለት ምን እንደሆነ ሲያብራሩ አንድ ሰው ከሰብዓዊ ተፈጥሮ በላይ አድርጎት የሚያመልከው ፤የሚከተለው ወይም የሚታዘዘው ማንኛውም ነገር ነው ብለዋል። ጣዖቶች በርካታ ሲሆኑ ቀንደኞቹ ግን አምስት ናቸው። ኢብሊስ (ዲያብሎስ)፤ መመለኩን ወዶ የተመለከበት ሰው፤ አምልኩኝ ብሎ ለሌሎች ጥሪ ያደረገ ሰው ፤ከሕዋስ የራቀውን ነገር(ጓይብን) አውቃለሁ የሚል እምነት ያለውና አላህ ያስተላለፈውን ሸሪዓ ትቶ በሰው ሰራሽ ሕግ የፈረደ ወይም ያስተዳደረ ሰው ናቸው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱ.ወ) ቃል ነው:-

55. አል-ነሕል(16):36

«በሃይማኖት ማስገደድ የለም፤ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፤ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው፤ ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፤ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።»[56]

የ«ላእላህ እል–ላል–ሏህ» ትርጉምም በአጭሩ ይኸው ነው። ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን የነቢዩ (ሰዐወ) ቃል እናገኛለን:-

«رأس الأمـر الإسـلام وعمـوده
الصلاة وذروة سنامه الجهاد في سبيل الله»

«የነገሩ ሁሉ ራስ እስላም ነው። ምሰሶው ሶላት ነው። ለእላዩ ጉልላቱ ደግሞ በአላህ መንገድ መታገል(ጅሃድ) ነው።»[57]

56. አል–በቀራህ(2):256
57. ጠበራኒ የዘገቡት ሐዲስ

# ለሰላት መሟላት ያለባቸው ነጥቦች (ሸርጦች) ዘጠኝ ናቸው

ለሶስት መሟላት ያለባቸው ነጥቦች(ሸርጥ) ዘጠኝ ናቸው። እነሱም:- ሙስሊም መሆን፣ የአእምሮ ጤንነት፣ ራስን ማወቅ የሚያስችል ዕድሜ (ሕፃን አለመሆን)፣ የተሟላ ንጽሕና፣ ከርከሰት (ከነጃሳ) መጥራት፣ ሀፍረተ ገላን(ዐውረት) መሸፈን፣ የሰላት ጊዜ መድረስ፣ ፊትን ወደ ቅብላ (መካ) አግጣጫ ማዞርና ለሶላት ቁርጠኛ ውሳኔ (ኒያ) ማድረግ ናቸው።

የመጀመሪያው ሸርጥ እስላም ሲሆን ተጻራሪው ክህደት(ኩፍር) ነው። ከሃዲ (ካፊር) የሆነ ሰው ደግሞ የፈለገውን ዓይነት ጽድቅ ቢሰራ ሥራው ተቀባይነት የለውም። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ مَا كَانَ لِلْمُشْرِكِينَ أَن يَعْمُرُوا مَسَاجِدَ اللَّهِ شَاهِدِينَ عَلَىٰ أَنفُسِهِم بِالْكُفْرِ ۚ أُولَٰئِكَ حَبِطَتْ أَعْمَالُهُمْ وَفِي النَّارِ هُمْ خَالِدُونَ ﴿١٧﴾ ﴾ سورة التوبة: ١٧.

﴿ وَقَدِمْنَا إِلَىٰ مَا عَمِلُوا مِنْ عَمَلٍ فَجَعَلْنَاهُ هَبَاءً مَّنثُورًا ﴾ سورة الفرقان: ٢٣

«ለከሓዲዎች፣ በነፍሶቻቸው ላይ በክሕደት የሚመሰክሩ ሲሆኑ፣ የአላህን መስጊዶች ሊሰሩ አይገባቸውም፣ እነዚህ ሥራዎቻቸው ተበላሹ፣ እነሱም በእሳት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው።»[58]

«ከሥራም ወደ ሰሩት እናስባለን፣ የተበተነ ትቢያም እናደርገዋለን።»[59]

---

58. አል–ተውባህ(9):17

59. አል–ፉርቃን(25):23

ሁለተኛው ሸርጥ ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው መሆን ሲሆን ተቃራኒው የአእምር ሕመም ወይም እብደት ነው። እብድ ሰው ደግሞ ከእብደቱ ተመልሶ እስከድንና ራሱን እስኪያውቅ ድረስ በሚፈጽመው ነገር ተጠያቂ አይሆንም። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ነው:-

«رفع القلم عن ثلاثة: النائم حتى يستيقظ
والمجنون حتى يفيق والصغير حتى يبلغ»

«ሶስት ሰዎች በኃላፊነት አይጠየቁም (ጥፋት አይጻፍባቸውም)፤ እነሱም:- የተኛ ሰው ከእንቅልፉ እስኪነቃ፣ ያበደ ሰው ከእብደቱ ተፈውሶ ራሱን እስኪያውቅ፣ ሕጻን ልጅ ኣቅመ አዳም (ሔዋን) እስኪደርስ።»[60]

ሶስተኛው ሸርጥ ራሱን ያወቀና ነገርችን የለየ ሰው መሆን ሲሆን ተቃራኒው ጨቅላ ሕጻንነት ነው። ይህ የዕድሜ ገደብም ሰባት ዓመት ነው፡፡ ሰባት ከሞላ ቀጥሎ በተመለከተው የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ መሰረት እንዲሰግድ ይታዘዛል:-

«مروا أبناءكم بالصلاة لسبع واضربوهم
عليهـا لعشر وفـرقـوا بينهم في المضـاجـع»

«ልጆቻችሁ ሰባት ዓመት ሲሞላ እንዲሰግዱ እዘዟቸው። (ካልሰገዱ) አስር ዓመት ከሞላቸው(እንዲሰግዱ) ምቷቸው፤ በምኝታም ለያዩዋቸው።»[61]

---

60. አሕመድ የዘገቡት ሐዲስ
61. አል-ሐኪም የዘገቡት ሐዲስ

አራተኛው ሸርጥ ንጽሕና ሲሆን እርሱም የታወቀው ውዱእ ነው። ውዱእ ማድረግን ግዴታ የሚያደርገው የውዱእ መፍረስ (ሐደስ) ሲሆን ውድእ በተራው አሥር መሥፈርት አሉት። እነዚህም ሙስሊም መሆን፣ የአእምሮ ጤንነት፣ ራስን ማወቅ የሚያስችል ዕድሜ ፣ ኒያ ማድረግ ማለትም ውዱኡ ተጀምሮ እስኪሟላ ድረስ ለማቋረጥ አለመወሰን(አለመነየት)፣ ከተጸዳዱ በኋላ ሽንቱ ሙሉ በሙሉ መንጠባጠቡ መቆም፣ ከተጻዳዱ በኋላ ብልቶችን በውሃና ከውሃ አስቀድሞ ደረቅ ባለ ነገር ማጽዳት፣ የሚጠቀሙት ውሃ ንጹሕ(ጣሀር) እና መጠቀሙ የተፈቀደ መሆን፣ ውሃ ወደ ቆዳ ዘልቆ እንዳይገባ የሚያግድ ነገር ካለ ማስወገድና ውዱእ የሚያፈርስ ነገር በማያቋርጥ ሁኔታ ለሚያጋጥመው ሰው የሶላቱ ጊዜ መድረስ ናቸው።

የውዱእ ግዴታዎች (ፈርድ) ስድስት ሲሆኑ እነሱም:- መጉመጥመጥና በአፍንጫ ውሃ ስቦ ማስወጣትን በሚያጠቃልል መልኩ ፊት መታጠብ፣ ይህም የራስ ፀጉር ከላይ በኩልና ከጎን ደርሶ ከቆመበት ወይም ከማይበቅልበት ከልል ጀምሮ ወደታች እስከ አገጭ ያለውን በጎን ከሁለቱ ጆሮዎች ከልል በመለስ ያለውን የፊት ክፍል ሙሉ በሙሉ ማዳረስ ነው። ከዚያም ሁለት እጆችን እስከ ክርን ድረስ ማጠብ፣ ሁለቱን ጆሮዎች አጠቃሉ ራስን ሙሉ በሙሉ በውሃ ማበስ፣ ሁለቱን እግሮች እስከ ቁርጭምጭሚቶች ማጠብና ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ሁሉንም ማከታተል ናቸው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا قُمۡتُمۡ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغۡسِلُواْ وُجُوهَكُمۡ وَأَيۡدِيَكُمۡ إِلَى ٱلۡمَرَافِقِ وَٱمۡسَحُواْ بِرُءُوسِكُمۡ وَأَرۡجُلَكُمۡ إِلَى ٱلۡكَعۡبَيۡنِ ﴾ الآية

سورة المائدة : ٦

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ! ፊቶቻችሁን እጆቻችሁንም! እስከ ክርናች እጠቡ። ራሶቻችሁንም (በውሃ) እበሱ። እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)!..»[62]

የወዱእ ተግባሮችን በቅድም ተከተላቸው መሰረት የማከናወን ማስረጃው:-

«ابداو بما بدأ الله به»

«አላህ (አንቀጹ ውስጥ) በጀመረው (ፊትን በመታጠብ) ጀምሩ» የሚለው የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ነው። ተግባሮቹን ሳያቆራርጡ የማከታተል ማስረጃው ደግሞ ነቢዩ (ሰዐወ) ወዱእ አድርጎ የመጣውን ሰውዬ እግሩ ላይ ውሃ ያልነካውና አንድ ድርሃም የሚሆን ደረቅ ቦታ አይተው ተመልሰህ ውዱእህን አሟላ ብለው ያዘዙት መሆናቸው ነው።»

የወዱእ ዋጂብ ደግሞ ሲጀመር ካስታወሱ « ብስምላ-ላህ» ብሉ በአላህ ስም መጀመር ነው።

ውዱእ የሚያበላሹ ነገሮች ዘጠኝ ናቸው:- እነሱም ከፊትና ከኋላ ብልቶች ወኩል ከሆድ የሚወጣ ማንኛውም ነገር፣ ከሌላው የአካል ክፍል በብዛት የሚወጣ(እንደ ደም) ያለ ነጃሳ ነገር፣ የፊትም ሆነ የኋላ ብልትን በእጅ መንካት፣ የግመል ሥጋ መብላት፣ የሞተ ሰው አስከሬን ማጠብ፣ አላህ ይጠብቀንና– እስላምን ከድቶ መቀልበስ ናቸው።

62. አል–ማኢዳህ(5):6

አምስተኛው ሸርጥ ርክስትን(ነጃሳን) ከሶስት ነገሮች ማለትም ከገላ ከልብስና ከመስገጃው ሥፍራ ማስወገድ ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ ﴾ سورة المدثر: ٤

«ልብስህንም አጥራ።»[63]

ስድስተኛው ሸርጥ ሀፍረተ ገላን (ዐውራ) መሸፈን ሲሆን መልበስ እየቻለ ራቁቱን የሰገደ ሰው ሶላቱ ውድቅ መሆኑን ሊቃውንት በአንድ ድምጽ ተስማምተውበታል። የወንድ ሀፍረተ ገላ ከብቢቱ እስከ ጉልበቱ መካከል ያለው የአካሉ ክፍል ነው። ሴት ባሪያም እንደዚሁ ከብቢቷ እስከ ጉልበቷ መካከል ያለው የአካሏ ክፍል ሀፍረተ ገላ (ዐውራ) ነው። ነፃ ሴት ደግሞ ከፊቷ በስተቀር መላ አካሏ ሀፍረተ ገላ (ዐውረት) ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ خُذُواْ زِينَتَكُمْ عِندَ كُلِّ مَسْجِدٍ ﴾ الأعراف: ٣١

«የአዳም ልጆች ሆይ! (ሀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ (በሶላት ከዕባን በመዞር ጊዜ ሸፍኑ) ያዙ..»[64]

ሰባተኛው ሸርጥ የሶላቱ ጊዜ መድረስ ሲሆን ማስረጃው መልአኩ ጅብሪል(ዐሰ) ነቢዩን (ሰዐወ) በኢማምነት በወቅቱ መጀመሪያና በወቅቱ መጨረሻ ላይ አሰግዶ ሙሐመድ ሆይ! ሶላት መስገድ በነዚህ በሁለቱ (በወቅቱ መጀመሪያና መጨረሻ) መካከል

63. አል–ሙደሲር(7):44
64. አል-አዕራፍ(7):31

ባለው ጊዜ ውስጥ ነው እንዳላቸው የተነገረበት ሐዲስ[65] ነው።
ሌላው ማስረጃ ደግሞ ቀጥሎ የተመለከተው የአላህ (ሱወ) ቃል :-

﴿ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ كَانَتۡ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ كِتَٰبًا مَّوۡقُوتًا ﴾

﴿ أَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ لِدُلُوكِ ٱلشَّمۡسِ إِلَىٰ غَسَقِ ٱلَّيۡلِ وَقُرۡءَانَ ٱلۡفَجۡرِۖ إِنَّ قُرۡءَانَ ٱلۡفَجۡرِ كَانَ مَشۡهُودًا ﴾ الاسراء : ٧٨

«..ሶላት በምእመናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናት።»[66]
«ሶላትን ከፀሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ጨለማ ድረስ ስገድ፤ የጎህንም ሶላት ስገድ፤ የጎህ ሶላት፡ (መላእክት) የሚጣዱት ነውና።»[67]

ስምንተኛው ሸርጥ በሶላት ወቅት ፊትን ወደ ቂብላ (መካ) አግጣጫ ማዞር ነው። ማስረጃው ቀጥሎ ያለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ قَدۡ نَرَىٰ تَقَلُّبَ وَجۡهِكَ فِي ٱلسَّمَآءِۖ فَلَنُوَلِّيَنَّكَ قِبۡلَةً تَرۡضَىٰهَاۚ فَوَلِّ وَجۡهَكَ شَطۡرَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِۚ وَحَيۡثُ مَا كُنتُمۡ فَوَلُّواْ وُجُوهَكُمۡ شَطۡرَهُۥ ﴾ البقرة : ١٤٤

«የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን፤ ወደ ምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን፤ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ከዕባ) አግጣጫ አዙር፤ የትም ሥፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ፤..»[68]

ዘጠነኛው ሸርጥ ኒያ(ቁርጠኛ ሃሳብ) ማድረግ ሲሆን የሚደረገውም በልብ ነው። ኒያውን በአንደበት አሰምቶ መናገር ግን ብድዓ(በሃይማኖቱ ውስጥ ያልነበረ አዲስ ሰው ሰራሽ ፈጠራ) ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የነቢዩ (ሰዐወ) ሐዲስ ነው:-

65. ሐዲሱን አሕመድ በሰፊው ዘግቦታል
66. አል-ኒሳእ(4):103
67. አል-ኢስራእ(17):78
68. አል-በቀራህ(2):144

«إنما الأعمال بالنيات وإنما لكل

امرىء ما نوى»

[1] «ሥራዎች (ግንኛቸውም) እሳህ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸው ከቁርጠኛ ፍላጎት የመነጩ ሲሆን ብቻ ነው። እያንዳንዱም ሰው በልቡ ባቀደው መሰረት(ምንዳ) ያገኛል።»[69]

## የሶላት ማዕዘናት (አርካን) አሥራ አራት ናቸው

እነሱም:- ችሎታ ያለው ሰው መቆም፤ «አሏሁ አክበር» ማለት፤ ፋቲሐ መድገም፤ ሁለቱን መዳፎች በሁለቱ ጎልበቶች ላይ በማሳረፍ ከወገብ በመታጠፍ ማጎንበስ(ሩኩዕ)፤ ከሩኩዕ ቀና ብሎ ወደ ነበሩበት አቋቋም መመለስ፤ ሰባቱን የአካል ክፍሎች ማለትም ግንባርን፤ ሁለቱን እጆች፤ ሁለቱን ጉልበቶችና የሁለቱን እግሮች ጣቶች መሬት በማስነካት ሱጁድ ማድረግ፤ ከሱጁድ ቀና ማለትና በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ፤ በሁሉም የሶላት ማዕዘናት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ በእርጋታ(በጡመእኒነህ) መቆየት፤ ቅደም ተከተሉን መጠበቅ፤ በሶላቱ መጨረሻ ላይ ለተሸሁድ (አት-ተሕያቱ ለመድገም) መቀመጥ፤ አላህ ለነቢዩ(ሰዐወ) በእክብሮት የተቀናጀ እዝነት እንዲሰጥ መለመንና ሶላቱን በሁለት ሰላምታ ማጠቃለል ናቸው።

69. ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

የመጀመሪያው ማዕዘን (ሩክን) የሚችል ሰው ሶላቱን ቆሞ ማከናወን ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ حَٰفِظُواْ عَلَى ٱلصَّلَوَٰتِ وَٱلصَّلَوٰةِ ٱلْوُسْطَىٰ وَقُومُواْ لِلَّهِ قَٰنِتِينَ ﴾

سورة البقرة: ٢٣٨

«በሶላቶች፣ (በተለይ) በመካከለኛይቱም ሶላት ላይ ተጠባበቁ፤ ታዛዦች ኾናችሁም ለአላህ ቁሙ።»[70]

ሁለተኛው ሩክን ለሶላት መግቢያ ተክቢራ(አሏሁ አክበር ማለት) ነው። ለዚህ ማስረጃው«(የሶላት) መግቢያው ተክቢራ ነው፤ መውጫው ደግሞ ሰላምታ(አስ-ሰላሙ ዓለይኩም ማለት) ነው» የሚለው የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ነው። ከተክቢራ በኋላ የመክፈቻ ጸሎት (እስትፍታሕ) ይደረጋል። ዱዓኡል እስትፍታሕ ሱንና ሲሆን እሱም የሚከተለው ነው:-

سبحانك اللهم وبحمدك وتبارك اسمك وتعالى.
جدك ولا إلــه غيرك)

«ሱብሓነከ አሏሁም-መ ወቢሐምድከ ወተባረከ እስሙከ ወተዓላ ጀድ-ዱከ ወላ ኢላሃ ጓይሩከ»

ትርጉሙ:- «አላህ ሆይ! ጥራት ይገባህ፤ ምሥጋና ላንተ ይሁን፤ ስምህ ብሩክ ነው፤ ልዕልናህም ላቀ፤ ካንተ በስተቀርም ሌላ አምላክ የለም።» ማለት ነው።

ጥራት ይገባህ ማለት ልሃያልነትህ የተገባ ጥራትና ቅድስና ይድረስህ ማለት ነው። ምሥጋና ይገባህ ማለት ሙገሳና ውዳሴ

70. አል-በቀራህ(2):238

ይድረስህ ማለት ነው። ስምህ ብሩክ ነው ማለት አንተን ማውሳት በረከት ያጎናጽፋል ማለት ነው። ልዕልናህ ላቀ ማለት አንተ ከሁሉም በላይ ሃያል ነህ ማለት ነው። ካንተ በስተቀርም ሌላ አምላክ የለም ማለት ደግሞ አላህ ሆይ! በምድርም ሆነ በሰማይ ካንተ በስተቀር የሚገገዙት እውነተኛ አምላክ የለም ማለት ነው። ከመክፈቻው ጸሎት በኋላ «አዑዙ ብል—ላህ ምነሽ—ሸይጣን ር־ረጂ־ም» ማለት ነው። ትርጉሙ «አሏህ ሆይ! ከእዝነትህ የራቀው እርጉሙ ሸይጣን በሃይማኖታዊ ጉዳይም ሆነ በዓለማዊው እንዳይጎዳኝ በአንተ እጠበቃለሁ» ማለት ነው። ከዚያም ፋቲሐን (የቁርአን የመክፈቻው ምዕራፍ አንድን) በያንዳንዱ ረከዓ መድገም የሶላት አንዱ ማዕዘን (ሩክን) ነው። ይህም ቀጥሎ በሰፈረው ሐዲስ መሰረት ነው:-

«لا صلاة لمن لم يقرأ بفاتحة الكتاب»

«የቁርአንን መክፈቻ(ምዕራፍ) ያልደገመ ሰው(ሶላት) አልሰገደም።»[71]

የአል—ፋቲሐ ምዕራፍ የቁርአን መሰረት ነው። እሱም የሚከተለው ነው:-

«ብስምል—ላህር—ረሕማኒ ር—ረሒም
አልሐምዱ ሊል—ላህ ረብ—ብልዓለሚን
አር—ረሕማኒ ር—ረሒም
ማሊክ የውምዲን
እይ—ያከ ነዕቡዱ ወእይ—ያከ ነስተዒን

---

71. ቡኻሪ የዘገቡት ሐዲስ

እህድነስ–ሲራጠል ሙስተቂ–ም
ሲራጠል–ለዚ–ነ አንዓምተ ዐለይህም
ጓይሪል መግዱ–ብ ዐለይህም ወለዷ ል–ሊ?ን»

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿١﴾
ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٢﴾ ٱلرَّحْمَٰنِ
ٱلرَّحِيمِ ﴿٣﴾ مَٰلِكِ يَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٤﴾
إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ ﴿٥﴾
ٱهْدِنَا ٱلصِّرَٰطَ ٱلْمُسْتَقِيمَ ﴿٦﴾
صِرَٰطَ ٱلَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ
ٱلْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا ٱلضَّآلِّينَ ﴿٧﴾

«በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በኾነው።
ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤
እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ፣
የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው።
አንተን ብቻ እንግገዛለን፤
አንተንም ብቻ ርዳታ እንለምናለን።
ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።
የነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን፣ በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ፣
(ምራን፤ በሉ)። »

ትንታኔው:- «በአላህ ስም..» ማለት በአላህ ስም ለመባረክ በርሱ ለመታገዝ በርሱ ስም መጀመር ማለት ነው። «ምሥጋና ለአላህ.. » ማለት ምሥጋናና ውዳሴ ሁሉ ለርሱ ይሁን ማለት ነው። «የዓለማት ጌታ .. » ማለት ዓለማት ከፈጣሪ ጌታ ከአላህ በስተቀር ያለውን ሁሉ የሚያመለክት ነው። እርሱም ሁሉንም ፍጥረታት የፈጠረ ጌታ ነው። «አል–ረሕማን» ማለት ርህራሄው መላውን ፍጥረታት የሚያቅፍ እጅግ በጣም ርህሩህ የሆነ ጌታ ማለት ነው። «ረሒማ–ም» ማለት አዘኔታው በተለይ ለምዕመናን የሆነ በጣም አዛኝ ጌታ ማለት ነው። ለዚህ ትርጉም ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿وَكَانَ بِالْمُؤْمِنِينَ رَحِيمًا﴾ سورة الأحزاب : ٤٣

«.. ለአማኞች በጣም አዛኝ ነው»[72]

«የፍርዱ ቀን ባለቤት..» ማለት ሁሉም ሰው እንደ ሥራው ጥሩ ከሆነ ጥሩ መጥፎ ሰርቶ ከሆነም መጥፎ ምንዳ የሚያገኝበት የምርመራና የውሳኔ ቀን ማለት ነው። ለዚህ ትርጉም ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا يَوْمُ ٱلدِّينِ ﴿١٧﴾ ثُمَّ مَآ أَدْرَىٰكَ مَا يَوْمُ ٱلدِّينِ ﴿١٨﴾ يَوْمَ لَا تَمْلِكُ نَفْسٌ لِّنَفْسٍ شَيْـًٔا ۖ وَٱلْأَمْرُ يَوْمَئِذٍ لِّلَّهِ ﴿١٩﴾ ﴾

«የፍርዱ ቀን ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ? ከዚያም የፍርዱ ቀን ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ? (እርሱ) ማንኛይቱም ነፍስ ለሌላይቱ ነፍስ ምንንም ማድረግን የማትችልበት ቀን ነው። ነገሩም ሁሉ በዚያ ቀን ለአላህ ብቻ ነው።»[73]

72. አል–አሕዛብ(33):43

73. አል–ኢንፊጣር(82):17–19

የሚከተለው የነቢዩ (ሰዐወ) ሐዲስም ሌላው ማስረጃ ነው:-

«الكيس من
دان نفسه وعمل لما بعد الموت والعاجز من أتبع نفسه
هواها وتمنى على الله الأماني»

«አርቆ የሚያስተውል አእምሮ ያለው ጠንቃቃ ሰው ስሜታዊ ዝንባሌውን (ነፍሱን) ታግሎ ከቁጥጥር ሥር በማዋል ከሞት በኋላ ላለው (ዘለዓለማዊ) ሕይወት የሰራ ሰው ነው። ደካማ ሰው ደግሞ በስሜታዊ ዝንባሌው ቁጥጥር ሥር ወድቆ በመገዛት ያለ ምንም ጥረት የአላህን ምህረት ለመቃደል ከንቱ ተምኔት የሚመኝ ሰው ነው።»[74]

«አንተን ብቻ እንገገዛለን!.. » ማለት ካንተ በስተቀር ማንንም ምንንም አናመልክም ማለት ሲሆን ከርሱ በስተተር ለሌላ ላለመገገዛት በፈጣሪ ጌታውና በባሪያው ፍጡር መካከል የተደረገ ቃል ኪዳን ነው። «አንተንም ብቻ ርዳታ እንለምናለን» ማለት ከርሱ በስተቀር ከሌላ ረድኤት ላለመለመን በጌታና በፍጡሩ መካከል የተፈጸመ ቃል ኪዳን ነው። «ቀጥተኛውን መንገድ ምራን» ማለት ቀጥተኛውን ጥመትና መዛነፍ የማይኖርበትን ሙሐመዳዊ ቁርአናዊ የእስላም ጎዳና ምራንና በርሱ ላይ የምንጸና አድርገን ማለት ነው። «የነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን..» ማለት ጸጋውን ያጎናጸፋቸው ምዕመናን መንገድ ማለት ሲሆን ማስረጃውም የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُو۟لَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنْعَمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ
ٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَ ۚ وَحَسُنَ أُو۟لَٰٓئِكَ
رَفِيقًا ﴾ سورة النساء: ٦٩.

74. አሕመድ የዘገቡት ሐዲስ

«አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው፤ እነዚያ ከነዚያ አላህ በነርሱ ላይ ከለገሰላቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም ፣ ከሰማዕታትም ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ። የነዚያም ጓደኝነት አማረ!» [75]

«በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና..» ማለት ዕውቀቱ ከአላህ ተላልፎላቸው እያለ ያልሰሩበትን አይሁዶች የሚያመለክት ነው። እንደ እነሱ ከመሆን እንዲጠብቀን አላህን እንለምናለን። «ያልተሳሳቱትንም ሰዎች..» ማለት ደግሞ በተመትና በማይምንት ላይ በተመሰረተ መንገድ አላህን የሚገዙትን ክርስቲያኖች የሚመለከት ነው። አላህ ከነሱ መንገድ እንዲያርቀን እንለምናለን። ለዚህ ማስረጃው ቀጥሉ የተመለከተው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ قُلْ هَلْ نُنَبِّئُكُم بِالْأَخْسَرِينَ أَعْمَالًا (١٠٣) الَّذِينَ ضَلَّ سَعْيُهُمْ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا
وَهُمْ يَحْسَبُونَ أَنَّهُمْ يُحْسِنُونَ صُنْعًا ﴾ سورة الكهف: ١٠٣

«:-በሥራዎች በጣም ከሳሪዎቹን እንንገራችሁን? በላቸው። እነዚያ እነሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ፤ በቅርቢቱ ሕይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው። »[76]

በነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ሁለትም የሚከተለውን እናገኛለን:-
«لتتبعن سنن من قبلكم
حذو القذة بالقذة حتى لو دخلوا جحر ضب
لدخلتموه قالوا يارسول الله اليهود والنصارى؟
قال فمن » أخرجاه والحديث الثاني «افترقت اليهود

75. አል–ኒሳእ(4):69
76. አል–ከሀፍ(18):103–104

على إحدى وسبعين فرقة وافترقت النصارى على اثنتين وسبعين فرقة وستفترق هذه الأمة على ثلاث وسبعين فرقة كلها في النار إلا واحدة، قلنا: من هي يارسول الله؟ قال: من كان على مثل ما أنا عليه وأصحابي»

«ከናንተ በፊት የነበሩትን ሕዝቦች (መንገድ) እርእያ የድብ ጉድጓድ ቢገቡ እንኳ እስከመግባት ድረስ በገቡበት ገብታችሁ ትከተላላችሁ።» የአላህ መልክተኛ ሆይ! አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ነው? ስንል «ታዲያ ሌላ ማን ይሆናል!» አሉ።

«አይሁዶች ሰባ አንድ ቦታ ተከፋፍለዋል። ክርስቲያኖች ደግሞ በሰባ ሁለት ቡድኖች ተከፋፍለዋል። ይህ ሕዝብ (ሕዝበ እስላም) ደሞ በሰባ ሶስት ቡድኖች ይከፋፈላል። ከዚያ ውስጥ አንዱ ቡድን ብቻ ሲቀር ሁሉም የእሳት ናቸው»።

የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይህች ቡድን የትኛዋ ነች? ብለን ስንጠይቅ «እኔና ባልደረቦቼ (ሰሓቦቼ) ዛሬ ያለንበትን መንገድ በመሰለ መንገድ ላይ የሆነ ሰው ነው» አሉ።

ከዚያም ሩኩዕ መውረድ ነው። ሩኩዕ ከወገብ ወደፊት በመታጠፍ ሁለቱን መዳፎች በሁለቱ ጉልበቶች ላይ አሳርፎ እንደቆሙ ማጎንበስ ነው። ተጥሉም ከሩኩዕ ቀና ብሎ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ተመልሶ መቆም፣ ሰባት የአካል ክፍሎችን መሬት በማስነካት ሱጁድ ማድረግ፣በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ቆይታ ማድረግ ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃልና የነቢዩ (ሰዐወ) ሐዲስ ነው:-

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ ءَامَنُوا ارْكَعُوا وَاسْجُدُوا﴾ الحج : ٧٧

«أمرت ان أسجد على

سبعة أعظم» والطمأنينة في جميع الأفعال. والترتيب

«እላንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! (በስግደታችሁ) አጎንብሱ፣ በግንባራችሁም ተደፉ! ..»[77]

«ሰባት አጥንቶችን (የአካል ክፍሎችን) መሬት በማስነካት ግንባሬን ደፍቼ እንድሰግድ ታዝዣለሁ።» [78]

«ነቢዩ ዘንድ ተቀምጠን እያለን አንድ ሰው መጣና ሰግዶ ካበቃ በኋላ ለነቢዩ(ሰዐወ) ሰላምታ አቀረበ። ነቢዩ(ሰዐወ) (ሰላምታውን ከመለሱ በኋላ) አሟልተህ አልሰገድክምና እንደገና ተመልሰህ ስገድ አሉት። (ሰውዬው ተመልሶ ሰግዶ ሲመጣም) አሁንም አላሟላህምና ተመልሰህ ስገድ ብለውት ሦስቴ መለሱት።»

ሰውዬው ሦስት ጊዜ ከተመላለሰ በኋላ እውነተኛ ነቢይ አድርጎ በላከዎ ጌታ እምላለሁ ከዚህ የበለጠ ማላመር አልችልምና አስተምሩኝ አላቸው። ነቢዩም (ሰዐወ) እንዲህ አሉት:-

إذا قمت الى الصلاة فكبر

ثم اقرأ ما تيسر معك من القرآن، ثم اركع حتى تطمئن راكعاً. ثم ارفع حتى تعتدل قائماً ثم اسجد حتى تطمئن ساجداً. ثم ارفع حتى تطمئن جالساً ثم افعل ذلك في صلاتك كلها».

77. አል– ሐጅ(22):77
78. ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

«ለመስገድ ተዘጋጅተህ ስትቆም (አሏሁ አክበር) በልና የተቻለህን ያህል ከቁርአን እንቀጾች አንብብ፤ ከዚያም ለሩኩዕ እጎንብስና በእርጋታ ጥቂት ጊዜ ቆይበት፤ ከዚያም ከሩኩዕ ቀና ብለህ ትንሽ ቆም በል፤ ከዚያም በግንባር መሬት ላይ በመደፋት ሱጁድ ውረድና በእርጋታ ጥቂት ጊዜ ቆይበት። ቀጥለህም ከሱጁድ ቀና ብለህ ለጥቂት ጊዜ ተቀመጥ፤ በሁሉም የሶላት ክፍሎች (ረከዓዎች) ውስጥ ይህንኑ አፈጻጸም በተመሳሳይ ሁኔታ ፈጽም።»

የመጨረሻው ተሸሁድ (አት—ተሕያቱ..) ቀጥሎ በሚቀርበውና ከእብኑ መስዑድ(ረዐ) በተዘገበው ሐዲስ ውስጥ እንደተመለከተው ሁሉ ግዴታ ከሆኑት የሶላት ግዕዘናት አንዱ ነው። ቀደም ሲል «ሰላም ከባሮች ለአላህ ይሁን ፤ ሠላም ለጅብሪል ለሚካኢል ይሁን እንል ነበር። ነቢዩ(ሳዐወ) ይህን ከልከለው ግለት ያለብንን ሲያስተምሩን እንዲህ አሉ:-

لا

تقولوا السلام على الله من عباده فإن الله هو السلام. ولكن قولوا: التحيات لله والصلوات والطيبات، السلام عليك أيها النبي ورحمة الله وبركاته، السلام علينا وعلى عباد الله الصالحين أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمداً عبده ورسوله

«ሠላም ከባሮቹ ለአላህ ይሁን አትበሉ። አላህ ራሱ ሰላም ነውና። ነገር ግን እንዲህ በሉ:- ክብር ሁሉ ጸሎት ሁሉ፤ መልካም ነገሮች ሁሉ የአላህ ናቸው። አንተ ነቢይ ሆይ ! ሰላም ለርስዎ ይሁን፤ የአላህ እዝነትና በረከቶቹም። ሰላም ለኛና ለደጋጎቹ የአላህ ባሮች ይሁን። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። መሐመድ የአላህ ባሪያና መልክተኛው መሆናቸውንም እመሰክራለሁ።»[79]

79. በቡኻሪ የዘገቡት ሐዲስ

«ክብር ሁሉ የአላህ ነው» ማለት እንደ ማጎንበስና በማንባር መዳፋት ያሉ የአክብሮት መግለጫዎች ሁሉ ለአላህ የሚገቡ የርሱ ንብረቶች ናቸው። የዓለማት ጌታ የሚከበርባቸው እንደ ዘላዓለማዊነት እንደ ቋሚነት ያሉ መከበሪያዎች ሁሉ የርሱ ናቸው ማለት ነው። ስለሆነም ከነዚህ ነገሮች አንዱንም ለሌላ ፍጡር አሳልፎ የሰጠ ሰው ሙሽሪክ ከሓዲ(ካፊር) ነው ማለት ነው። «ጸሎት ሁሉ» ማለት ሁሉም ዓይነት ጸሎቶች መቅረብ ያለባቸው ወይም አምስቱ ዕለታዊ የግዴታ ሶላቶች የሚቀርቡት ለአላህ ብቻ ነው ማለት ነው። «መልካም ነገሮች» ማለት አላህ መልካሙን ቃልና ተግባር ብቻ እንጂ አይቀበልም፣ የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጮም እርሱ ነው ማለት ነው። «አንተ ነቢይ ሆይ! ሰላም.. » ማለት ደግሞ ሰላም እዝነትና በረከት ለነቢዩ እንዲደርስ መጸለይ ነው። የሚጸለይለት ሰውም መለኮታዊ ባህሪ ሊኖረው አይችልም። «ሰላም ለኛና.. »ማለት ለራስህና በሰማይም ይሁን በምድር ለሚገኙ የአላህ ቅን አገልጋይ ሁሉ መጸለይ ሲሆን ደጋግ የአላህ ባሮች (ሷሊሖች) ይጸለይላቸዋል እንጂ ከአላህ ጋር አምልኮት አይደረግላቸውም ማለት ነው።» ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ.. » ማለትም ከአንድ አላህ በስተቀር በሰማይም ይሁን በምድር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ እውነተኛ አምላክ አለመኖሩን በፍጹምነትና በእርግጠኝነት መመስከር ማለት ነው። «ሙሐመድ የአላህ ባሪያና መልክተኛው ..» ማለት ደግሞ ነቢዩ የማይመለኩ የአላህ ባሪያ፣ የማይስተባበሉ የአላህ መልክተኛ፣ ትዕዛዛቸውን በቅንነት መፈጸምና ፈለጋቸውን እርምጃ በእርምጃ ተከትሎ መራመድ ግዴታ መሆኑንና አላህ(ሱወ) በቅን አገልጋይነት ያከበራቸው መሆኑን መመስከር ማለት ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿ تَبَارَكَ ٱلَّذِى نَزَّلَ ٱلْفُرْقَانَ عَلَىٰ عَبْدِهِۦ لِيَكُونَ لِلْعَـٰلَمِينَ نَذِيرًا ﴾ سورة الفرقان : ١

«ያ ፉርቃንን (ውነትን ከውሸት ለይውን መጽሐፍ) በባሪያው ላይ ፤ ለዓለማት አስፈራሪ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ)፤ ክብርና ጥራት ተገባው።..»[80]

ከዚያም የሚከተለውን ከተሸሁድ ማስከተል:-

اللهم صل
على محمد كما صليت على إبراهيم إنك حميد مجيدٌ

«አሏሁም—መ ሶል—ል ዐላ ሙሐመድን ከማ ሶል—ለይተ ዐላ ኢብራሂመ እን—ነከ ሐሚ—ዱን መጂ—ድ።»

ትርጉሙ:- «አላህ ሆይ! ለኢብራሂም እንዳደረከው ሁሉ አክብሮትና ውዳሴህን ለሙሐመድ አድርግ።» ማለት ነው።

«የአላህ ሶላት ለእገሌ ይሁን ማለት ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ እንደ ተመለከተው ሁሉ በላእላዩ መለኮታዊ ዓለም አላህ(ሱወ) አንድ ባሪያውን ወዶ ማሞገሱ ነው። የአላህ እዝነት (ረሕመት) ነው የሚሉም አሉ። ሆኖም ግን የመጀመሪያው ትርጉም ነው ትክክለኛ የሚሆነው። መላእኮች ሶላት አወረዱ ማለት ደግሞ ለዚያ ሰው ከአላህ ምህረት ለመኑ ማለት ነው። ሰዎች በሌሎች ላይ ሶላት አወረዱ ማለት ደግሞ ጸሎት አደረጉላቸው ማለት ነው። ከላይኛው ሰለዋት ቀጥሎ «ወባሪክ ዐላ ሙሐመድን..» የሚለው ክፍል ግን ግዴታ ሳይሆን ከአንደበታዊና ተግባራዊ ሱን—ናዎች የሚደመር ነው።

80. አል—ፉርቃን(25):1

የሶላት ግዴታዎች (ዋጂባት) ስምንት ሲሆኑ እነሱም:- ከመጀመሪያው የሶላት መክፈቻ(ከተክቢረቱል እሕራም) «አሏሁ አክበር» ውጭ ያሉ የተቀሩት ተክቢራዎች ፣ ሩኩዕ ሲደረግ የሚባለው «ሱብሐነ ረብ–ቢያል ዐዚም» ፣ ከሩኩዕ ቀና ሲባል በኢማሙም ሆነ በተከታዩ የሚደገመው «ሰሚዐል–ሏሁ ልመን–ሐምዳህ» «ረብ–በና ወለከል ሐምዱ» የሚለውም፣ ሱጁድ ውስጥ የሚደገመው «ሱብሐነ ረብ–ቢየል አዕላ» ፣ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል የሚባለው «ረብ–ብግፍርሊ» ፣ በሁለተኛው ረከዓ ላይ የሚደረገው የመጀመሪያው ተሸሁድ «አት–ተሕይ–ያቱ..» እና ለዚህ ተሸሁድ መቀመጡ ናቸው የሶላት ዋጂባት። የሶላት ማዕዘናት (ሩክን) ተረስቶ ወይም ሆን ተብሎ ከሶላቱ ከተጓደለ ሶላቱ ውድቅ ይሆናል። የሶላት ዋጅብ የሆነ ተግባር ከሶላት ውድቅ ሲሆን በመዘንጋት ከጎደለ ግን በማካካሻ ሱጁድ(ሱጅድ አል– ሰህው) ይካካሳል።

# አራቱ መሰረታዊ ሕጎች

የታላቁ ዐርሽ ጌታ የሆነው ቸሩ አላህ በዛሬዋ የዱንያ ሕይወትና በነገው ቀሪ ሕይወት ውዴታውን እንዲለግስህ፣ በሁሉም ሥፍራ ብሩክ እንዲያደርግህ፣ ሲያገኙ ከሚያመሰግኑ፣ መከራ ሲገጥማቸው ደግሞ ከሚታገሱና ኃጢአት ሲፈጽሙ ቶሎ ምህረት ከሚለምኑ ደጋግ አማኞች አንዱ እንድያደርግህ እለምነዋለሁ። እነዚህ ሶስት ነገሮች የተድላ (የሰዓዳ) ምልክት ናቸው። አላህ ትዕዛዙን ለመፈጸም እንድትችል ይምራህና የኢብራሂም ሃይማኖት የሆነው ሐኒፊይ–የህ(ወደ እውነት አዘንባይነት) አንድ አላህን ብቻ ሃይማኖትን ለርሱ ፍጹም በማድረግ ማምለክ መሆኑን እወቅ። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿ وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴾ سورة الذاريات : ٥٦

«ጋኔንና ሰውንም ፣ ሊገገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።»[1]

አላህ እንድትገገዛው(ዕባዳ እንድታደርግለት) የፈጠረህ መሆኑን ካወቅህ ማንኛውም ዕባዳ ከተውሒድ (የአላህን አንድነት ከማረጋገጥ) ጋር ካልሆነ በስተቀር ዕባዳ ወይም አምልኮተ አላህ ተብሎ መጠራት እንደማይቻል ዕወቅ። ልክ ሶላት ያ.. ጧሃራ(ያለውዱእ) ሶላት ተብሎ መጠራት እንደማይችል ሁሉ ዕባዳም ያለ ተውሒድ ዕባዳ ተብሎ መሰየም አይችልም። ከአላህ ጋር ፍጡራንን ማጋራት ወይም ሽርክ ዕባዳ ውስጥ ከገባ ጧሃራን የሚያፈርስ ነገር ሲከሰት ውዱእ እንደሚበላሸውና ውድቅ እንደሚሆነው ሁሉ ዕባዳውም ውድቅ ይሆናል። ሽርክ ዕባዳ

1. አል–ዛሪያት(5):56

(አምልኮተ አላህ) ውስጥ ከገባ ዕባዳውን ውድቅ ሥራን ቁርሽ በማድረግ ባለቤቱን ለዘለዓለም እሳት ውስጥ ነዋሪ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ከተገነዘብክም አላህ(ሱወ) ከዚህ የሽርክ መረብ ነጻ እንዲያወጣህ ማድረግ ያለብህ ዋነኛው ነገር ይህን አቢይ ነጥብ ማወቅና መረዳት ነው። ይህንኑ በማስመልከት አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል: - ﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغْفِرُ :

أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ﴾

النساء ١١٦،

«አላህ በርሱ ማጋራት አይምርም፣ ከዚህም ወዲያ ያለውን ለሚሻው ሰው ይምራል።..»[2]

ይህም አላህ(ሱወ) በቅዱስ መጽሐፉ ውስጥ ያወሳቸውን አራት መሰረታዊ ሕጎች በማወቅ ነው። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

## አንድኛው መሰረታዊ ሕግ

የመጀመሪያው መሰረታዊ ሕግ የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) የተዋጓቸው ካፊሮች አላህ(ሱወ) ፈጣሪ ሲሳይ ሰጭና የክስተቶች ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም አስተናባሪ መሆኑን ያረጋግጡ እንደነበረ ማወቅና ይህ ዕውቅናቸው ብቻውን ከእስላም ጎራ ያላስገባቸው መሆኑን መረዳት ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَيَعْبُدُونَ مِن

دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمْ وَلَا يَنفَعُهُمْ وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا

عِندَ ٱللَّهِ ﴾ سورة يونس : ١٨

2. አል-ኒሳእ(4):116

«ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ፣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው? በላቸው፤ በእርግጥም አላህ ነው ይሉሃል፤ ታዲያ(ለምን ታጋራላችሁ?) አትፈሩትምን? በላቸው።»[3]

## ሁለተኛው መሰረታዊ ሕግ

እነኛ ከሓዲዎች ጣዖታትን የምናመልከውና የምንማጸነው ወደ አላህ በነርሱ አገናኝነት ለመቅረብና አማላጅ እንዲሆኑን በማሰብ ብቻ ነው ይላሉ። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَىٰ إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِي مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ كَاذِبٌ كَفَّارٌ ﴾ سورة الزمر: ٣.

«..እነዚያም ከርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙ፣ ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም፣ (ይላሉ)፤ አላህ በዚያ እነርሱ በርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል፤ አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም።»[4]

---

3. ዩኑስ(10):31
4. አል-ዙመር(39):3

የምልጃ(የሸፋዓ) ማስረጃ ደግሞ የሚከተለው ነው:-

وَيَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمْ وَلَا يَنفَعُهُمْ وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا
عِندَ ٱللَّهِ ﴾ سورة يونس: ١٨

«ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይገዛሉ፤ እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ፤ ..»[5]

ምልጃ ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው ተቀባይነት የሌለው ምልጃ ሲሆን ሌላው ደግሞ ተቀባይነት ያለውና የተረጋገጠው ምልጃ(ሸፋዓ) ነው። ተቀባይነት የሌለው ምልጃ ከአላህ በስተቀር ማንም ፍጡር ማድረግ የማይችለውን ነገር ፍጡራን አማላጅ እንዲሆኑ የሚጠየቅበት የማማለድ ዓይነት ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَنفِقُوا۟ مِمَّا
رَزَقْنَٰكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ يَوْمٌ لَّا بَيْعٌ فِيهِ وَلَا خُلَّةٌ وَلَا شَفَٰعَةٌ
وَٱلْكَٰفِرُونَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴾ سورة البقرة: ٢٥٤.

«እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ውስጥ ሸያጭ፣ (መበዠት) ወዳጅነትም ፣ ምልጃም፣ የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ነገር ለግሱ፤ ከሓዲዎችም በዳዮቹ እነርሱ ናቸው።»[6]

ተቀባይነት ያለውን የተረጋገጠው ምልጃ(ሸፋዓ) ደግሞ ከአላህ የሚጠየቀው በዚህ ምልጃ አማላጅ የማማለድ ሥልጣኑን ከአላህ የሚያገኝ ሆኖ የሚያማልድለት ሰው ደግሞ አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ቃሉም ሆነ ተግባሩ የተወደደ ሰው መሆን ይኖርበታል። ይህም ሆኖ ግን ምልጃው (ሸፋዓው) በአላህ ፈቃድ ብቻ የሚፈጸም ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:- ﴿ مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ
إِلَّا بِإِذْنِهِۦ ﴾ سورة البقرة: ٢٥٥

5. ዩኑስ (10):8

6. አል-በቀራህ(2):254

«..እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ፣ ማነው? ..»[7]

## ሦስተኛው መሰረታዊ ሕግ

ነቢዩ (ሰዐወ) ትምህርታቸውን የጀመሩት የተለያዩ አምልኮት በሚያካሂዱ ሰዎች መካከል ነበር። መላእኮችን የሚያመልኩ፣ ነቢዮችንና ጻድቃንን የሚያመልኩ፣ በዛፎችና በድንጋዮች የሚያመልኩና ፀሐይ የሚያመልኩም ነበሩባቸው። የባ ዕድ አምልኮ የሚያካሄዱ ሰዎችን አንዱን ከሌላው ሳይለዩ ነበር የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ሁሉንም የተዋጉት። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ إِذْ تَسْتَغِيثُونَ رَبَّكُمْ
فَاسْتَجَابَ لَكُمْ ﴾ الآية سورة الأنفال: ٩.

«እውከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ፣ ተጋደሉዋቸው፤ ..»[8]

ፀሐይና ጨረቃ ያመልኩ እንደነበረ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَمِنْ ءَايَـٰتِهِ ٱلَّيْلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ لَا تَسْجُدُوا۟
لِلشَّمْسِ وَلَا لِلْقَمَرِ وَٱسْجُدُوا۟ لِلَّهِ ٱلَّذِى خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمْ إِيَّاهُ
تَعْبُدُونَ ﴾ سورة فصلت: ٣٧

«ሌሊትና ቀንም፣ ፀሐይና ጨረቃም፣ ከምልክቶቹ ናቸው፤ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፤ ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፤ እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደኾናችሁ፣ (ለሌላ አትስገዱ)።»[9]

7. አል–በቀራህ(2):255

8. አል–አንፋል(8):39

9. ሐ.ሚም. አል–ሰጅደህ(41):37

መላእኮችን ያመልኩ እንደነበረ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ وَلَا يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُوا الْمَلَائِكَةَ وَالنَّبِيِّينَ أَرْبَابًا ﴾

سورة آل عمران : ٨٠

«መላእክትንና ነቢያትንም አማልክት አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ፣ (አይገባውም)፤ »[10]

ነቢያትን ማምለካቸውን በተመለከተ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

وَإِذْ قَالَ اللَّهُ يَا عِيسَى ابْنَ مَرْيَمَ أَأَنتَ قُلْتَ لِلنَّاسِ اتَّخِذُونِي
وَأُمِّيَ إِلَٰهَيْنِ مِن دُونِ اللَّهِ قَالَ سُبْحَانَكَ مَا يَكُونُ لِي أَنْ
أَقُولَ مَا لَيْسَ لِي بِحَقٍّ إِن كُنتُ قُلْتُهُ فَقَدْ عَلِمْتَهُ تَعْلَمُ مَا فِي
نَفْسِي وَلَا أَعْلَمُ مَا فِي نَفْسِكَ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّامُ الْغُيُوبِ ﴿١١٦﴾

سورة المائدة: ١١٦

«በርሱ ያዘዝከኝን ቃል፡ ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፤ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም፤ በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፤ በተሞላኸኝ ጊዜ፣ (በነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፤ አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።»[11]

ጻድቃንን ያመልኩ እንደነበረ የሚያረጋግጠው ማስረጃ የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

---

10. አሊ-ዒምራን(3):80
11. አል-ማኢደህ(5):116

﴿ أُولَٰئِكَ الَّذِينَ يَدْعُونَ

يَبْتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ الْوَسِيلَةَ أَيُّهُمْ أَقْرَبُ وَيَرْجُونَ رَحْمَتَهُ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُ ﴾ الآية سورة الاسراء : ٥٧

«እነዚያ እነርሱ የሚገገዟቸው፣ ማገናኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን(ሥራ) ይፈልጋሉ፤ እዝነቱንም ይከጅላሉ፤ ቅጣቱንም ይፈራሉ፤ ..»[12]

በዛፎችና በድንጋዮች ያመልኩ እንደነበረ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ(ሱወ) ቃልና የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ነው:-

﴿ أَفَرَءَيْتُمُ

اللَّاتَ وَالْعُزَّىٰ ﴿١٩﴾ وَمَنَاةَ الثَّالِثَةَ الْأُخْرَىٰ ﴾ الآية سورة النجم : ١٩ ـ ٢٠

«አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን፣ (አያችሁን? የምትገገዟቸው ኃይል አላቸውን?)»[13]

በአቡ ዋቅድ አል-ዋቅድ አል-ለይሲ አማካይነት ከነቢዩ(ሰዐወ) የተላለፈው ሐዲስ ደግሞ የሚከተለው ነው:-

وحديث أبي واقد الليثي رضي الله عنه قال : «خرجنا مع النبي ﷺ إلى حنين ونحن حدثاء عهد بكفر، وللمشركين سدرة يعكفون عندها وينوطون بها اسلحتهم، يقال لها ذات أنواط فمررنا بسدرة فقلنا : يارسول الله اجعل لنا ذات أنواط كما لهم ذات أنواط» الحديث

12. አል-እስራእ(17):37
13. አል-ነጅም(53):19—20

«ኩፍር ትተን ከሰለምን ብዙ ያልቆዩን በነበርንበት ጊዜ ከነቢዩ (ሰዐወ) ጋር ወደ ሑነይን ሄድን። እዚያም ሙሽሪኮች የሚያመልኩበትና መሳሪያዎቻቸውን የሚያንጠለጥሉበት ‹ዛት አንዋጥ› የሚባል የቁርቁራ ዛፍ ነበራቸው። ዛፉ አጠገብ ስናልፍ የአላህ መልክተኛ ሆይ! እነርሱ ‹ዛት አንዋጥ› እንዳላቸው ሁሉ ለኛም «ዛት አንዋጥ» እንዲኖረን ያድርጉልን አልናቸው!..»[14]

# አራተኛ መሰረታዊ ሕግ

የዘመናችን ሙሽሪኮች የሽርክ ተግባር ከቀደምቶቹ የከፋ ከባድ ነው። የቀድሞው ዘመን ሙሽሪኮች ችግርና ጭንቅ በሌለበት ጊዜ በአላህ አሻርከው በችግርና በጭንቀት ወቅት ግን ሽርኩን ይተው ነበር። የዘመናችን ሙሽሪኮች ግን ሽርካቸው ቋሚና በደስታም ሆነ በችግር ወቅት የሚቀጥል የማያቋርጥ ሽርክ ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿ فَإِذَا رَكِبُوا۟ فِى ٱلْفُلْكِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ ﴾ سورة العنكبوت : ٦٥.

«በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም፤ አላህን፤ መገገዛትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል፤ ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ።»[15]

---

14. ትርምዚ የዘገቡት ሐዲስ
15. አል–ዐንከቡት(29):65